1 አዎ።   የለም/አይደለም።   አላውቅም።   አልገባኝም።

2 ሥመዎ ማን ነው?   ሥመዎን በእንግሊዝኛ ሊጽፉት ይችላሉ?

3 እባከዎ አድራሻዎን ይጻፉ።

4 እድሜዎ ሥንት ነው?

5 በሥልክም ሆነ በሌላ መንገድ ልንገናኘው የምንችለው ሰው ሥምና የስልክቁጥር ወይም አድራሻ ሊሰጡን ይችላሉ?

6 በጥቂት ጊዜ ውስጥ ይመረመራሉ   [1]በዶክተር።   [2]በነርሥ።

7 አደጋ/ግጭት አጋጥሞዎት ነበር?   መቸ? (በቀን መቁጠሪያውና በሰዓቱ ላይ በማሳየት)

8 ራሰዎን ስተው ነበር?

9 መቸ ነው የታመሙት? (በቀን መቁጠሪያውና በሰዓቱ ላይ በማሳየት)

10 የህመም ስሜት አለዎት?   የት ላይ እንደሆነ ያመልክቱ።   መቸ ነው የጀመረዎት?
(በቀን መቁጠሪያውና በሰዓቱ ላይ በማሳየት)

11 **የሕመሙ ደረጃ ምን ያህል ነው?**   1 **(ሕመም ከሌለህ)**   2   3   4   5   6   7   8   9   10 **(ቀጣይ ሕመም)**

12 ህመሙ፣ ቋሚ ነው   ወይስ ሄድ መለስ የሚል?

13 የደም መፍሰስ ሁኔታ አለበዎት?   የት ላይ እንደሆነ ያመላክቱ።

14 ሣል አለበዎት?   ሲያስለዎት የሚወጣዎት ነገር አለ?
ምን አይነት ቀለም አለው?   ነጭ?   ቢጫ-አረንጓዴ?   ቀይ?   ቡናማ?

15 ትንፋሽ ያጥረዎታል?

16 አስታውኮዎታል?   ደም ኣስታውኮት ያቃል ወይ?

17 ተቅማጥ ነገር አለዎት?

18 የሆድ ድርቀት አለበዎት?

19 ጥቁር ሽንት ተፀዳድተው ያቃሉ ወይ?

20 ቁርጭምጭሚተዎ ያብጣል?

21 ክብደት ቀንሰዋል?

22 በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ችግር አለበዎት?   [1]የማይየት?   [2]የመስማት?   [3]የመዋጥ?   [4]የመራመድ?

23 ኦፐራሲዮን (ቀዶ-ህክምና) ተደርገው ያውቃሉ?   የቱ ላይ እንደሆነ ያመልክቱ።

24 የመጨረሻው የወር አበባዎ የጀመረው መቸ ነው? (በቀን መቁጠሪያው ላይ በማሳየት)
እርጉዝ ነዎት?   የስንት ወር እርግዝና?
እርጉዝ ሊሆኑ ይችላሉ ወይ?   የእርግዝና ምርመራ ማድረግ እንችላለን?

25 ያጨሳሉ?   በቀን ስንት ሲጋራ?

26 ከሚከተሉት ውስጥ የትኞቹ አሉበዎት?   [1]የስኳር በሽታ?   [2]የሚጥል በሽታ?   [3]አስም?

27 ከሚከተሉት ውስጥ በየትኞቹ ተይዘው ያውቃሉ?   [1]የልብ ችግር?   [2]የልብ ህመም?   [3]ከፍተኛ የደም ግፊት?
[4]የልብ ድካም?   [5]የደም መርጋት በሽታ?   [6]የወፍ በሽታ?   [7]የጉበት እብጠት (ሄፓታይቲስ)?

28 የማይስማማዎት (አልርጂክ የሚሆንበዎት) መድሃኒት አለ?   ፔኒሲሊን?   አስፒሪን?   ሌላ ዓይነት መድሃኒት?

29 በአሁኑ ሰዓት የሚወስዱት መድሀኒት አለዎት?   ለዓይነት አሁን የያዙትአለ?
ሌሎች ዓይነት መድሃኒቶችን ወይም የተፈጥሮ፡ባህላዊ መሀኒቶችን ይወስዳሉ?

30 ስንት ያህል ከኒን ወስደዋል?

31 በቅርቡ የቴታነስ ክትባት ተክትበዋል?

32 በቅርብ ጊዜ ከዩቿኬ ውጪ ወደሌላ ሀገር ሄደው ነበር? የተ ሀገር? መቸ?

33 እኔ [1]ነርስ ነኝ:: [2]ዶክተር ነኝ:: [3]የመጀመሪያ እርዳታ ሰጪ ነኝ:: [4]የድንገተኛ ሁኔታ ሀኪም ነኝ::
[5]የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኛ ነኝ::

34 ምርመራ እንዳደርግለዎት ይፈቅዱልኛል? [1]በወንድ [2]በሴት ቢመረመሩቅር ይለዎታል?

35 ይቅርታ፣ ይህ ህመም እንዲሰማዎት ሊያደርግ ይችላል::

36 የደም ግፊት ኃይለዎን መለካት እፈልጋለሁ::

37 የልብ ምተዎን በደረተዎ ላይ ማዳመጥ እፈልጋለሁ::

38 የልበዎን ሁኔታ መመርመር እፈልጋለሁ::

39 የውስጥ ምርመራ ሳደርግለዎት እፈልጋለሁ::

40 መርፌ ልሰጠዎት/ልወጋዎት እፈልጋለሁ::

41 ይሄን ቱቦ ወደውስጥ ልልከው/ልሰደው እፈልጋለሁ::

42 የደመዎን ናሙና መውሰድ እፈልጋለሁ::

43 ወደ ራጅ ክፍል ልልከዎት እፈልጋለሁ::

44 ጥቂት የሚሰፉ ነገሮችን በክር/በቀጭን ሽቦ ልሰፋለዎት እፈልጋለሁ::
የተሰፋውን ክር ለማስወጣት በ----ቀን (በቀን መቁጠሪያውና በሰዓቱ ላይ በማሳየት) ወደሀኪመዎ መሄድ ይኖርበዎታል::

45 [1]በእግረዎ [2]በቁርጭምጭሚትዎ [3]በእጅዎ [4]በእጅ አንጓዎ [5]በትከሻዎ ላይ ውልቃት/ስብራት አለበዎት::

46 [1]በእግረዎ [2]በቁርጭምጭሚትዎ [3]በእጅዎ [4]በእጅ አንጓዎ ላይ የጥገና ጀሶ እንዲታሰርለዎት ያስፈልጋል::

47 ይህንን (በማመልከት) እስከ (በቀን መቁጠሪያው ላይ በማሳየት) ድረስ ጠብቀውማቆየት ይኖርበዎታል::

48 እባከዎ ውሃ በዚህ መያዣ ውስጥ ያፍስሱ::

49 ምንም ነገር አይብሉ ወይም አይጠጡ::

50 አሁን ሊነሱ ይችላሉ::

51 በሆስፒታል ውስጥ መቆየት ይኖርበዎታል::
እባከዎ በዋርዱ ውስጥ አልጋ እስከሚገኝለዎት ድረስ ይጠብቁ::

52 ሁሉም ነገር ይስተካከላል:: አያስቡ::

53 ታክሲ ልጥራለዎት?

54 እርዳታ ከፈለጉ ይህን ይጠቀሙ::

55 እባከዎ ይጠብቁ:: በዚህ በኩል ይምጡ:: ወደቤተዎ መሄድ ይችላሉ::

56 ተጨማሪ ችግር ካለበዎት እባከዎ ተመልሰው ይምጡ::

57 እንደገና ልድገምለዎት ...

## ጥያቄ ከታካሚዎች

58 ለምን ያክል ጊዜ እጠብቃለሁ? እስከ 1 ሰዓት እስከ 2 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት እስከ 4 ሰዓት

59 ስሜን የሚጠራ ሰው ይኖራል?

60 ስልክ የት ጋ ነው ያለው? ለቤተሰቤ/ለጓደኛየ መደወል እፈልጋለሁ?

61 እባከዎ ወደቤቴ እንዲሄድ ታክሲ ሊጠሩልኝ ይችላሉ?

62 ከእንግዲህ ደህና እሆናለሁ?